


| | |
|---|---|
| የወንበር እሽቅድድም የ TMO ስታይል | ሁሌ ማን እንደሚያሸንፍ ይገምቱ |

## **KCTMO – FOI** ሁለት ወሬ እና ባለሁለት አይነት የህግ ትግበራ

የ TMO ኩባንያ ጸሀፊዎች መካከል Sinead McQuillan የመጨረሻዋ ነች፣ ከአስራሁለት አመት በፊት በ2005 በ KCTMO የተዘጋጀውን ሪፖርት እንዲሰጠኝ የጠየኩትን ጥያቄ ውድቅ በማድረግ ከጥቂት ቀናት በፊት ኢሜል ልካልኛለች። በወቅቱ እኔ የ Lancaster West Estate አስተዳደር ቦርድ አባል ነበርኩ እና ሪፖርቱ የተዘጋጀው በ Grenfell ህንጻ ላይ የሚገኙት ሁለት ሶስተኛው የአደጋ ጊዜ መብራቶች ክፍሎች በ TMO የተደረገውን መደበኛ ምርመራ መውደቃቸውን ካወቅን በኋላ ከ EMB በተደረገ ከፍተኛ ጫና ነው።

የመብራት ክፍሎቹ በአደጋ ጊዜ የሚጠቀሙት የባትሪ እሽጎች ኤሌክትሪክ በሚቋረጥበት ወቅት እና ከፍተኛ የእሳት አደጋ ቢነሳ እና ህንጻውን መልቀቅ አስፈላጊ ቢሆን ጊዜያዊ መብራት እንዲሰጡ ተደርገው የተሰሩ ናቸው። ሁለት ሶስተኛው የአደጋ ጊዜ መብራቶች የማይሰሩት የባትሪ እሽጋቸው የአገልግሎት ጊዜያቸው ስላለፈበት እንዲሁም ለብዙ አመታት

ጥገናም ሆነ ቅያሪ ያልተደረገለት ስለሆነ ነው። EMB ይህን ጉዳይ በወቅቱ አንገብጋቢ ጉዳይ አድርጎት ነበር። በ TMO የተዘጋጀው የአማካሪዎቹ ሪፖርት ከእኛ አስተያየት ጋር ተመሳሳይ ነበር፤ እንዲሁም TMOን እና ኮንትራክተሮቹን በጣም ነቅፎ ነበር። TMO ለበርካታ ወራት ያልተቀበለውን የ EMB ቅሬታ መሰረት ያለው እና የተረጋገጠ ሆኖ አግኝቶታል።

የጠየኩትን የሪፖርት ቅጂ በጁላይ 14 ወ/ሪት McQuillan የከለከለችበት ምክንያት TMO ሀላፊነቱ የተወሰነ ኩባንያ ስለሆነ የመረጃ ነጻነት ህግ ስለማይመለከተው ነው ብላለች። በ McQuillan እና እኔ መካከል የተደረገውን የኢሜል ልውውጥ ዝርዝር ከዚህኛው በፊት የብሎግ(ጡመራ) ማሳያው ላይ ይባዛል፡ "KCTMO - የመኖሪያ ቤት አስተዳደር ለህዝቡ፣ በህዝቡ?" KCTMO የመረጃ ነጻነት ህግ መተላለፋቸውን እና በተዘዋዋሪ የሚቆጣጠሩትን በኮሚቴው ባለቤትነት የተያዘውን የማህበር ቤቶች ውስጥ ያሉትን ደንበኞቻቸውን ባለማክበራቸው 'የተከራይ አስተዳደር ድርጅት' ነን የሚሉትን አቋም አልተገበሩትም። ከ RBKC ኮሚቴው ጋር ተስማምቶ በመስራት የቅሬታ ቦርድ እና ለ EMB አባላት (ማለትም በ TMO ለረዥም ጊዜ የተጨቆኑ እና ድምጽ የሌላቸው) ቀደም ብሎ ከተፈቀደው አነስተኛ መጠን አንጻር የተጋነነ ክፍያ የሚከፍሉት በክፍያ የተመረጡ ተከራይ አባላት ላይ አሁንም ያላቸው የይስሙላ ውክልና ነው።

ኮሚቴው መጥፎው KCTMO ከመፈጠሩ ከብዙ አመት በፊት በ1993 ከ EMB ጋር የገባውን የአስተዳደር ስምምነት አለማክበር ከኮሚቴው ስምመነት ጋር ተደምሮ KCTMO የ EMB ስልጣን በሙሉ ሊወስድበት የሚችል ሁኔታ ፈጥሯል። በእኛ እና የ TMOን የብዙ አመት ብቁ አለመሆን እና ቸልተኝነት የቻሉ አብዛኛው የ TMO ነዋሪዎች አስተያየት መሰረት የተከራይ ቦርድ አባላት ራሳቸው ለሚሰሩት የ TMO ቢሮክራሲ (በሚያገለግለው ኮሚቴ የሚደገፍ እና እንዲሰራ የተደረገ እንዲሁም ትንሽም እንኳን ህጋዊነት ወይም ህልውና የሌለው ነው፤ ይህ ደግሞ በደንበኞቹ ዘንድ ለብዙ አመታት የሚታወቅ እውነታ ነው እንዲሁም ጁን 14 Grenfell ህንጻ ላይ በደረሰው አደጋ በገሀድ የተጋለጠ ነው) የውሸት ማረጋገጫ ለመስጠት ብቻ የተቀመጡ 'የቁስል ቅርፊት' ናቸው።

ስለዚህ የመረጃ ነጻነት ህጉ ምን ሆነ? ከእሳት አደጋ ደህንነት እና ሌላ የጤና እና የደህንነት ጉዳዮች ጋር የተያያዘ መረጃ በኮሚቴው ባለቤትነት የሚተዳደር የመኖሪያ ቤት ነዋሪዎች መስጠት እንዳለበት በሚያስገምት ደንቦች መሰረት?

The KCTMO website includes a page entitled ‘**Access to Information**’ which, until very recently, contained the following statements:

**"የመረጃ ጥበቃ ህግ 1998 (DPA), የመረጃ ነጻነት ህግ 2000 (FOI) እና የአካባቢ ሁኔታ መረጃ ደንቦች 2004 (EIR) ነዋሪዎች እና የህዝቡ ተወካዮች በመንግስት ባለስልጣናት እና ለመንግስት ባለስልጣናት የተያዙ መረጃዎችን ለመጠየቅ ያስችላሉ።**

**በ RBKC ምትክ የሚሰጡ አገልግሎቶችን በተመለከተ በ KCTMO ለ RBKC የተያዘ መረጃ ሲጠየቅ መረጃው ካለ በጽሁፍ መስጠት አለብን።”**

[የ TMO የመረጃ ተደራሽነት እትም 01]

የ FOI ጥያቄዎን McQuillan ውድቅ ካደረገቸው ከጥቂት ቀናት በኋላ የገጹ ይዘት እንደሚከተለው ሆኖ ተቀየረ፡

**"TMO የግል ተቋም ቢሆንም እንዲሁም የ FOI ተገዢ ባይሆንም እንኳን RBKC የህግ እና የደንብ ግዴታውን ለመወጣት አስፈልጎት (በ FOI ስር ያለውን መንኛውንም ግዴታ ጨምሮ) የሚጠይቀውን ማንኛውንም መረጃ ለ RBKC መስጠት አለብን።**

**TMOን FOI በቀጥታ ባይመለከተውም በራሱ የተጠያቂነት አጀንዳ መሰረት ይሰራል። ይህ ማለት TMO ሲችል መረጃ ይሰጣል ነገር ግን ምክንያታዊ ሆኖ ሲያገኘው መረጃ የመስጠት መብቱን ይገድባል፤ ለምሳሌ የ TMO የንግድ መብትን/ፍላጎትን ወይም ሶስተኛ ወገን መብትን/ፍላጎትን ለማስጠበቅ ወይም መረጃ መስጠቱ የወንጀል፣ የደንብ ወይም ሌላ ምርመራን የሚያስተጓጉል ከሆነ።”**

[የ TMO የመረጃ ተደራሽነት እትም 02]

በዲሰምበር 2014 የ Grenfell Action Group ብሎግ (ጡመራ) አጋር አዘጋጅ Edward Daffarn በመረጃ ነጻነት ህግ መሰረት ታቅዶ የነበረውን የ Grenfell ህንጻ ማሻሻያ ስራዎች ውይይት የተደረገባቸው ጉዳዮችን አስመልክቶ በ TMO ፣ ኮንትራክተራቸው፣ Rydon እና የፕሮጀክቱ አርክቴክት፣ Studio E መካከል የተደረገውን ወርሃዊ ስብሰባ ቃለ-ጉባኤ

ቅጂ KCTMOንን ጠይቋል። ጥያቄው በ McQuillan የበላይ Fola Kafidya ውድቅ ተደርጓል፤ የተገለጸው ምክንያት፡

*"…. የተጠየቀው መረጃ በመንግስት ባለስልጣኑ ወይም በመንግስት ባለስልጣኑ ወኪልነት በ TMO የተያዘ መረጃ ስላልሆነ ከመረጃ ነጻነት ህግ 2000 ነጻ የተደረገ (የተገለለ) ነው። የመረጃ ነጻነት ህግ 2000 የሚመለከተው በመንግስት ባለስልጣኑ ወኪልነት የተያዘ መረጃን ነው።*

በሚገርም ሁኔታ ወ/ሪት Kafidya በዛው የኢሜል ጽሁፍ ላይ በመረጃ ነጻነት ህጕ ላይ የተጠቀሱትን ጥቅት ማግለያዎች (ክፍል 43 ንዑስ ክፍል 2) የሚከተለውን በማለት አንስታለች፡

*" TMO ከኮንትራክተሮቹ ጋር የሚያደርገው የንግድ ንግግሮች/ውይይቶች ጥንቃቄ የሚያስፈልገው ጕዳይ ስለሆነ ይህን መረጃ መስጠት የኮንትራክተሩን የንግድ መብት/ፍላጎት ሊጎዳው ይችላል። “*

ከዚህ በመነሳት ቀጣዩ ጥያቄ ይነሳል፡ KCTMO ለመረጃ ነጻነት ህግ ተገዢ አይደለም ብላ Kafidya የእውነት ካመነች መረጃው በህጕ ንዑስ ክፍል እንደማይካተት መናገር ለምን አስፈለጋት፤ ይህ በግልጽ የሚያሳየው KCTMO ለመረጃ ነጻነት ህጕ ተገዢ እንደሆነ እንደምታምን ነው?

የወ/ሪት Kafidyaንን በግልጽ ግራ የተጋባ የውሳኔ መሰረት አቶ Daffarn ባለመቀበል መልሷል፤ ይኸውም የ TMO ብቸኛ ሚና ወይም ስራ በአካባቢያዊ ባለስልጣን፣ የ Kensington እና Chelsea የከበርቴ ሰፈር ባለቤትነት የተያዙ የመኖሪያ ቤት ክምችትን ማስተዳደር ነው እና የሚይዙት ሁሉም መረጃ በአካባቢያዊ ባለስልጣን ወኪልነት የተያዘ ነው፤ ስለሆነም ከህጕ ነጻ ሊሆን አይችልም። አቶ Daffarn በዚህ መሰረት ውድቅ የተደረገበትን ግልጽ ለማድረግ ግምገማ ጠይቋል።

በጥቂት ቀናት ውስጥ (ማለትም ህግ የሚያስገድደውን ትክክለኛ እና ዝርዝር ግምገማ ለማድረግ በማያስችል አጭር ጊዜ ውስጥ) ከወ/ሪት Kafidya የመጨረሻ ክልከላ ደረሰው። በሚያስገርም ሁኔታ TMO ከመረጃ ነጻነት ህግ ውጪ ነው እያለች ታስመስል የነበረውን ሁሉ ትታ አሁን ደግሞ ለ TMO ክልከላው የሚከተለውን ምክንያት ሰጥታለች፡

*" TMO ከኮንትራክተሮቹ ጋር የሚያደርገው የንግድ ንግግሮች/ውይይቶች ጥንቃቄ የሚያስፈልገው ጕዳይ ስለሆነ ይህን መረጃ መስጠት የኮንትራክተሩን የንግድ መብት/ፍላጎት ሊጎዳው ይችላል። "* በመረጃ ነጻነት

ህግ ክፍል *43(2)* መሰረት እንደዚህ አይነት መረጃ ከመስጠት የታገደ ነው። በመሆኑም የጠየቁትን መረጃ ልንሰጥ አንችልም። በመረጃ ነጻነት ህግ ***2000*** መሰረት ይህ ኢሜል እንደ ክልከላ ማስታወቂያ ያገለግላል።“

አቶ Daffarn ለወ/ሪት Kafidya ቆይቶ በሜይ 2016 ሌላ የ FOI ጥያቄ አቅርቦ ነበር። የጠየቀው RBKC ላይ ለመኖሪያ ቤት እና ንብረት ምርመራ ኮሚቴ በ TMO የቀረበውን የሪፖርት ቅጂ ነበር። በዚህኛው ዙር ደረሰው ቀና መልስ ነበር።

*Fola Kafidiya-Oke FCIS*
የአመራር ሀላፊ እና የኩባንያው ጸሀፊ
የ *Kensington & Chelsea* የከበርቴ ሰፈር
የተከራይ አስተዳደር ድርጅት*"*

ወ/ሪት Kafidya KCTMO የመንግስት አካል ነው ወይስ አይደለም ወይም የመረጃ ነጻነት ህግ ተገዢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውም በተመለከተ ቀደም ብሎ የነበራትን ጥርጣሬ ወይም አለመግባባት አሁን ግልጽ ያደረገች ይመስላል። በርግጠኝነት TMO የመንግስት አካል መሆኑን እና የ FOI ህግ ተገዢ መሆኑን ተረድታለች።

ለአቶ Daffarn የተላከው የመጨረሻው ማሳወቂያ በኃላ ትንሽ ቆይታ ከ TMO ስራ ለቀቀች ነገር ግን አሁን የ Linkedin ፕሮፋይሏ በ KCTMO በአመራ ሀላፊ እና የኩባንያ ጸሀፊ ሆና ስትሰራ ስለነበራት ቆይታ የሚለውን ማየት አስገራሚ ነው። እንዲህ ይላል፡

*"…የመረጃ ጥበቃ ህግ፣ የመረጃ ነጻነት ህግ እና ሌሎች የመንግስት አካላት የሚይዙትን መረጃ ተደራሽነት ጋር የተያያዙ ህጎችን ማረጋገጥ።"*

https://uk.linkedin.com/in/folakafidiya

KCTMO ዛሬም፣ ሁሌም የመረጃ ነጻነት ህግ ተገዢ እንደነበር የሚያሳይ ማስረጃ በ FOI እትም ስርአት (የመንግስት አካላት ህገ ማክበር እንዳለባቸው የሚያስገድድ) ውስጥ ይገኛል፤ ይህ እትም ለመጀመሪያ ጊዜ የታተመው በ2005 በ TMO ሲሆን ከ TMO ድህረ-ገጽ ላይ ማውረድ ይቻላል። ማስታወሻ፡ ምናልባት አዲሱ የኩባንያው ጸሀፊ ይህን ብሎግ አንብቦ፣ ከ TMO ድህረ-ገጽ ላይ ይህን ሰነድ በማጥፋት ሌላ ነገር መጻፍ ካሰበ ቀደም ብለን ያወረድነውን ቅጂ ጭነነዋል፡

TMO_freedom_of_information_publication_scheme

የ Fola Kafidya መልቀቅ እና በ Sinead McQuillan መተካትን ተከትሎ TMO በመረጃ ነጻነት ላይ ያለው አቋም ተመልሶ ወደነበረበት ተመልሷል፤ ከትንሽ ለውጥ ጋር። ይኸውም Kafidya ይዛው የነበረው የመጀመሪያ አቋም ማለትም በ FOIA መሰረት TMO ሀላፊነት ያለበት በአካባቢያዊ ባለስልጣን ውክልና የያዙትን መረጃ ለመስጠት ብቻ ነው ይል የነበረው አቋም አሁን የአካባቢያዊ ባለስልጣኑ በ FOIA መሰረት ያለበትን ሀላፊነት መወጣት እንዲችል ይህን መረጃ መስጠት ያለብን ለመንግስት ሳይሆን ለአካባቢያዊ ባለስልጣን ለራሱ ነው በሚለው በ McQuillan አቋም ተቀይሯል።

ነገር ግን እኔ እስከሚገባኝ ድረስ የጠየኩት የ2005 ሪፖርት በኮሚቴው ይዞታ ስር ሆኖ አያውቅም እንዲሁም ሪፖርቱ ላይ የተገለጹት ምክሮችን የመተግበር ሀላፊነት የኮሚቴው ሳይሆን ሪፖርቱን በመጀመሪያ ደረጃ ያዘጋጀው የ TMO ነበር። ሪፖርቱ ላይ የተገለጹት ምክሮች የ Grenfell ህንጻ የአደጋ ጊዜ መብራት ስርአቱ ሙሉ በሙሉ እንዲቀየር እና የተሻሻለ የምርመራ ስርአት እንዲሁም የአዲሱ ስርአት ምርመራ እንዲደረግ ብለው ነበር። ከእነዚህ ምክሮች የመጀመሪያው ተተግብሮ ነበር ነገር ግን የተሻሻለ የምርመራ ስርአት ስለመኖሩ በጣም አጠራጣሪ ነው፤ ከነበረም ለረዥም ጊዜ የተተገበ አልነበረም። የ TMO የአስተዳደር ባህልን በተመለከተ መሰረታዊ ለውጦች እንዲደረጉ ተመክረው ነበር፤ ከዛ የሆነውን ሁላችንም እናውቃለን። ናዳ! ዚልች! ስናፉ!

የ **TMO** ነዋሪዎች ሁሉም ተሸናፊ የሚሆኑበት ግራየሚያጋባ ያወንበር እሽቅድድም ጨዋታ ላይ ነን፤ ምክንያቱም የጨዋታውን ህጎች የሚያወጣው እና የሚተረጉመው **TMO** ስለሆነ። ይህ የመረጃ ነጻነት ህግን፣ **TMO** አንዳንዴ በብልጠት የሚቀበላቸው ሀላፊነቶች እና **TMO** የመንግስት አካል አይደል ስለሆነም ለሚያገለግለው መንግስት እና የመኖሪያ ቤት አገልገሎት (የእሳት አደጋ ደህንነት እና ሁሉም የጤና እና ደህንነት አገልግሎቶችን ጨምሮ) ለሚሰጠው ሰው ተጠያቂ ሊሆን አይችልም በሚል የውሸት ምክንያት ውድቅ የሚያደርጋቸው ሀላፊነቶች ያካትታል።

ይህ የወንበር እሽቅድድም ጨዋታ በፍጹም አያሳቅም። በጁን **14** በጣም ብዙ ሰዎች በአሰቃቂ ሁኔታ ሞተዋል። በዛ ምሽት ወገኖቻቸውን ያጡት እና 'የተረፉት' ሰዎች ክፉኛ ተጎድተዋል፤ ያ ምሽት ካሳረፈባቸው የህሊና ጠባሳ ጋር እስከ ህይወታቸው መጨረሻ ድረስ አብረው ይኖራሉ። ይህን ሁሉ ባስከተለውን የወንጀል ቸልተኝነት ውስጥ የተዘፈቀው **KCTMO** ያለውን

መረጃ ላለመስጠት ያለውን ምክንያት ሁሉ እየተጠቀመ አሁንም አብሮን አለ።

## አሁን ደግሞ መልስ ፍለጋ ማን ጋር መሄድ አለብን?

## Martin Moore-Bick ጋር?  አይመስለኝም!